ቁቻነሰ ቁ 5

*የመጀመሪያ ረቂቅ። ~~ይፋ የማይሆን~~ - ለውስጥ ውይይት የቀረበ*

# ከኢህአዴግ ቧልት 2002 ባሻገር!!

ከምርጫ 2002 ቀርቶ ወደፊትም ቢሆን ከማንኛውም በኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ስር ከሚደረግ ምርጫ ተብየ ቧልት እኛም ህዝባችንም ምንም የምንጠብቀው በጎ ነገር የለም። አይኖርምም። ከግንቦት 97 በኋላ የታየውን የሸብር ሂደትና የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የህዝብን ፍላጎት ተፃርረው በስልጣን ለመቆየት ያሳዩትን "ቁርጠኛነት" በሚገባ እኛም ህዝባችንም እናውቀዋለን። ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ከሩቅም ቢሆን "መድበለ ፓርቲ" የሚመስል ምርጫ ለማዘጋጀት ቢጥሩም ከእንግዲህ በዚህ ስርአት ስር የሚካሄድ ምርጫ በቶታሊቴርያን ስርአቶች ስር እንደታዘብነውና አሁንም እንደምንታዘበው ህዝባችን በየአምስት አመቱ በገፍ እየወጣ ለዚህ ስርአት "ያለውን ድጋፍ" ለማደስ የሚገደድባቸው ወቅታዊ ስነስርአቶች እየሆኑ እንደሚሄዱ መጠራጠር አይቻልም። በመሆኑም የእኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችም ትግል በየአምስት አመቱ ገርበብ እያለች በምትከፈት በር ተጠቅሞ እያገረሸ ወዲያዉኑ ደግሞ የሚከስም ግርግር እንዳይሆን ከፈለግን በሶስት ጥያቄዎች ዙሪያ ተወያይተን ለሃገራችንና ለህዝባችን የሚጠቅም የትግል ስልት ማውጣት ያስፈልገናል።

መጀመሪያ ነገር ይህ ኢህአዴጋዊ ቧልት ለአሸባሪው አገዛዝ ትንሽም ብትሆን ይበልጥ ተአማኒነትን አስገኝቶ፣ ህዝባችንን ይበልጥ ግራ አጋብቶ፣ የሃገራችንን ዴሞክራቶች ይበልጥ ከፋፍሎ ቀጣዩን ትግል ይበልጥ የአቀበት ጉዞ እንዳያደርግብን ምን ስትራቴጂ እንከተል በሚለው ጥያቄ ዙሪያ መወያየት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ለሚሉት ቅጥፈት ህዝብንና በተለይ ደግሞ አለም አቀፍ ኮሙኒቲውን ለማደናገር የሚጠቀሙባቸውን ነጥቦች ከወዲሁ "ተንብየን" በሰፊና የተቀነባበረ ቅስቀሳ ማጋለጥ ይኖርብናል።

ሁለተኛ ከ2002 ዘልቀን በጠቅላላው በአምባገነን ስርአቶች ስር ከሚካሄዱ ምርጫዎች አንፃር በአንድ በኩል "ሁሉ ነገር ከምርጫ" በሌላ በኩል ደግሞ "ምርጫ ብሎ ነገር እርም" ከሚሉ ሁለት ፅንፈኛ አካሄዶች ባሻገር እንዲህ አይነቱ ሂደት በአንድ ህዝብ የዴሞክራታይዜሽን ትግል የሚጫወተውን ወይም ሊጫወት የሚችለውን አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ሚና በጥሞና አመዛዝነን ይህንን ትግል ከማደናቀፍ ይልቅ ሊያግዝ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል።

ሶስተኛ ከዚህ በመነሳት የሃገራችን ዴሞክራቶች ከግንቦት ቅልበሳ ጋር የከሰመውን ህዝባዊ የትግል እምርታ ለመቀስቀስ በቀጣዩ ምርጫ ምን አይነት ተሳትፎ ያድርጉ በሚለውና እንዳለፈው ልምዳችን ይህ የተቀሰቀሰ እምርታ ተመልሶ እንዳይከስም ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል በሚለው ጥያቄ ዙሪያ መወያየት ያስፈልጋል።

## 1. የኢህአዴግን የግራ ማጋቢያ ነጥቦች ስለ ስለማጋለጥ

የኢህአዴግ መሪዎችን የቆየ ክርክር እናውቀዋለን። " ዛሬ በሃገራችን ለነፃና ፍትሃዊ መድበለ ፓርቲ ምርጫ የተመቻቸ ህገመንግስታዊም ፖለቲካዊም ሁኔታ አለ። ግንቦት 97ም ቢሆን እንደዚሁ ነበር። ከተቃዋሚው ወገን አንዳንድ 'አክራሪዎች' በምርጫ ሲሸነፉ ይህንን መቀበል ስላልፈለጉ ስልጣን በጎዳና ነውጥ ለመጨበጥ በአመፅ ተሰማሩ። ህገ መንግስታዊውን ስርአት ለመጠበቅ እርምጃ ለመውሰድ ተገደድን። አሁን እንደዚያ አይነት ቀውስ እንዳይፈጠር ከተቃዋሚዎች ጋር የስነ ምግባር ስምምነት ተፈራርመን እንከን የለሽ መድበለ ፓርቲ ምርጫ እናካሂዳለን።" የሚል ነው። እንደዚህ አይነቱን ቅስቀሳቸውን ለማጎልበት ቢያንስ በአራት የማደናገሪያ አቅጣጫዎች ይሰማራሉ ብሎ መጠበቅ ይቻላል። እነዚህ ምንድን ናቸው? የኛስ የዴሞክራቶች አፀፋ ምን ሊሆን ይችላል?

የመጀመሪያው የማደናገሪያ ነጥብ የህዝብን "ሰፊ ተሳትፎ" የሚመለከተው ቅስቀሳቸው ይሆናል። አንዳንድ ተቃዋሚዎች የቦይኮት ጥሪ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ከኢህአዴግ ጋር ቆመው ህዝባችን በዚህ ሂደት በሰፊው እንዲሳተፍ ቅስቀሳ ማድረጋቸው አይቀርም። በዚህ ሁኔታ የኢህአዴግ መሪዎች "አንዳንድ አክራሪዎች የቦይኮት ጥሪ

ቢያደርጉም ህዝቡ ግን በሂደቱ አምኖበት በነቂስ ወጥቶ ድምፁን ሰጠ" ለሚሉት ፕሮፓጋንዳ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ ግልፅ ነው። "ማመቻቸት" ማለት ደግሞ ዛሬ በተተከለው የሽብር ስርአት በከተማም ሆነ በተለይ ደግሞ በገጠር በዚህ ሂደት ያልተሳተፈ ዜጋ በተቃዋሚነት ተፈርጆ ቅጣት ስለሚጠብቀው "በገፍ" ወጥቶ የግዱን እንዲሳተፍ ይደረጋል ማለት ነው። ይህንን "ድህረ ግንቦት" ሊባል የሚችል አዲስ ክስተት ከወዲሁ አይተነዋል። ህዝቡ ከዳር እስከዳር እምነት በጣለበትና ተቃዋሚ ሃይሎችም በሰፊው በተንቀሳቀሱበት በግንቦት 97 ምርጫ ከተመዘገበው መራጭ 82% ድምፁን ሰጥቶ እንደነበረ ይታወሳል። በአለፈው የማሟያና የወረዳ ምርጫ ምንም አመኔታ ባልነበረበትና ተቃዋሚዎችም ቦይኮት ባደረጉት ሂደት ግን ከመራጩ ህዝብ 93% ተሳትፎ ነበር ተብሏል። ነገም ከዚህ የተለየ ነገር አይኖርም። ይህ ሁኔታ በውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ምንም አይነት ውዥንብር እንዳያስከትል ከፈለግን ቅስቀሳችን ከወዲሁ በሁለት ነጥቦች ላይ ማተኮር ይኖርበታል። አንደኛ ተሳትፎን በተመለከተ እንደ ድምፅ ቆጠራው የፈለጉትን አሃዝ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ሁለተኛ ትላንት በደርግና በቀድሞ ሶሻሊስት ካምፕ እንደታየው ዛሬም እንደ ሰሜን ኮርያ አይነት አገሮች እንደምናየው ቶታሊታርያን ስርአቶች ስር ምርጫ መብት ሳይሆን ግዴታ ነው። በአጭሩ የህዝባዊ ተሳትፎ ተብየው ብዛት ብቻውን የግድ የአንድን የምርጫ ሂደት ነፃና ፍትሃዊ መሆን የሚያሳይ መስፈርት እንዳልሆነ ከወዲሁ በሰፊው ማብራራት ይኖርብናል።

ሁለተኛው የማደናገሪያ ነጥብ የምርጫውን ውጤት የሚመለከት ይሆናል። አሁን እንደሚታየው በተቃዋሚው ጎራ ኢህአዴግ በቀጣዩ ምርጫ 99% ያሸንፋል እየተባለ በእርግጠኝነት "የመተንበይ" አካሄድ የተያዘ ይመስላል። ይህ አጉል አቅጣጫ ነው። ያለቀለት ምርጫ ነው፣ ኢህአዴግ ከዚህ ምርጫ በማያወላዳ ሁኔታ በአሸናፊነት መውጣቱ የማያጠራጥር ነው ሲባል ይህንን አባባል በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል። ከአመት ተኩል በፊት ማሟያና የክልሎች ምርጫ በተባለው ቧልት እንደተደረገው በምርጫ 2002 የኢህአዴግ ተወዳዳሪዎች ለውድድር ከቀረቡት መቀመጫዎች ከዘጠና በመቶ በላይ "እንዲያሸንፉ" የሚሞከር አይመስለንም። የወያኔ ኢህአዴግ መሪዎች ለማይፈቅዷቸው ተቃዋሚዎች እዚህ ግባ የማይባል ለሚስማሟቸው ተቃዋሚዎች ደግሞ ከራሳቸው አልፈው ለነሱም "እንደሚያጭበረብሩላቸውና" ከፍተኛ ቁጥር ያለው መቀመጫ እንደሚለቁላቸው በዚህም የተነሳ በቀጣዩ "መድበለ ፓርቲ" ፓርላሜንት "አክራሪዎቹ" ተሸንፈው "የሰከኑ ተቃዋሚዎች" እንደዋና የተቃውሞ ሃይል ሆነው ብቅ ሊሉ የሚችሉበትን ሁኔታ እንደሚያመቻቹ መጠበቅ ይኖርብናል። ይህ አካሄድ በአንድ በኩል "ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ አልነበረም ወያኔ/ኢህአዴግ 99% መቀመጫዎችን ያሸንፋል" የሚሉትን ወገኖች ክርክር ውድቅ ለማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ "ዴሞክራሲ በሂደት የሚገነባ ነው" የሚለውን ማወናበጃቸውን ለማጠናከር ይጠቅማቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የነዚህ ተቃዋሚዎች የቁጥራቸው መጨመር ምንም ሳይፈይድ መድበለ ፓርቲ ስርአትና ነፃ ምርጫ ለሚለው ልፈፋቸው በአለም አቀፍ አሳዳሪዎቻቸው ፊት ይበልጥ ተአማኒነት ለማስገኘት ይረዳል።

ይህንን ስትራቴጂያቸውን ከወዲሁ ካላጋለጥን ነገ ከማንም አምባገነን ስርአት ስር የሚካሄድ ምርጫ እንደሚጠበቀው ሳይሆን ኢህአዴግ ህገ መንግስቱን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን ሁለት ሶስተኛ መቀመጫ ይዞና የቀረውን ለተቃዋሚዎች ለቆ "የሚመስል" ውጤት ቀምሞ ቢያቀርብ ህዝባችን ትንሽ ግራ የሚጋባበትና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲም ፊት ሂደቱ ትንሽ ተአማኒነት የሚያገኝበት ሁኔታ ሊከተል ይችላል። እዚህም ላይ የኛ ዋና ተግባር ይህንን አካሄድ ከወዲሁ ተንብየን "የህዝብ ተሳትፎ" ተብየው ነገር ብቻውን የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መስፈርት እንዳልሆነ ሁሉ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ በህዝብ ድምፅ ሳይሆን በኢህአዴግ መልካም ፈቃድ የሚለቀቅ መቀመጫ ብዛት የዴሞክራሲ መለኪያ እንዳይደለ ማጋለጥ ያስፈልጋል።

ሶስተኛው የማደናገሪያና በተለይ የውጭ ሃይሎችን ቀልብ ለመሳብ የሚደረገው ፕሮፓጋንዳ ምርጫው ገዥው ፓርቲና "የሰከኑ" ተቃዋሚዎች የስነ ምግባር ስምምነት በተፈራረሙበት ሁኔታ የሚካሄድ ስለሆነ ሰላማዊና እንከን የማይወጣለት ሂደት ነበር በሚለው ነጥብ ዙሪያ የሚቃኝ እንደሚሆን መጠበቅ ይኖርብናል። በእርግጥም የግንቦት 2002 ምርጫ ሂደት እንከን የለሽና ከአመፅ የፀዳ ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ አንዳንዶች "ታሪካዊ" እያሉ ለማሞካሸት የሚቃጣቸው የስነ ምግባር ስምምነት ስለተፈረመ አይደለም። መጀመሪያ ነገር ልብ ብሎ ለሚመለከት ዜጋ በስምምነቱ የተወሱት እንደ ነፃ ፕሬስ መረጋገጥ፣ እንደ ሰላማዊ ሰልፍና ህዝባዊ ስብሰባዎች አለመታገድ፣ እንደ ፖሊሱ፣ ሰራዊ

ቱ፣ አስተዳደሩና ፍርድ ቤት ተቋሞች ገለልተኛ መሆንና የመሳሰሉት ነጥቦች ከስራ ላይ አልዋሉም እንጂ ከወዲሁ በህ
ገመንግስቱም በምርጫ ህጉም ቢሆን "የተረጋገጡ" ናቸው። ምንም አዲስ ነገር የላቸውም። ለነዚህ ዴሞክራሲያዊ እ
ሴቶች መተግበር ዋናውና ብቸኛው እንቅፋት የኢህአዴግ መንግስት እንደሆነ መወሳትም እንኳን የሚገባው ነጥብ አይ
መስለንም። በመሆኑም በዚህ ሰነድ አማካኝነት የአብየ እከክ በእምየ ተላኮ እንጅኔር ሃይሉ ሻውል የፕሬስ ነፃነትን ለማ
ክበርና ጋዜጠኞችን ላለማዋከብ ቃል ስለገቡ፣ አቶ ልደቱ አያሌው ምርጫ ጣቢያዎችን በመሳሪያ ላለመውረር፣ ሰላማ
ዊ ሰልፎችንና ስብሰባዎችን ላለማገድ፣ መራጩን ህዝብ ላለማስፈራራት ስለተስማሙ፣ አቶ አየለ ጫሚሶ ያለኝን ስል
ጣን ተጠቅሜ መደለያ አላቀርብም፣ ቅጣትንና ማንኛውንም የማስፈራሪያ መንገድ አልጠቀምም፣ የፌዴራል መንግስትን
፣ የክልል መስተዳደርን፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤትን ወይም ሌላ የህዝብ ሃብት ለምርጫ ቅስቀሳ አላውልም ብለው ስለፈረ
ሙና ከሁሉም በላይ ምፀታዊ በሚመስለው የስምምነት ነጥብ ደግሞ "የህዝባችንን ውሳኔ በመፃረር በመንግስት ስልጣን
ላይ ለመቆየት ላለመሞከር" ቃል ስለገቡ ለነዚህ እሴቶች ተግባራዊነት ምንም የሚያደርገው አስተዋፅኦ አይኖረውም።

ከዚህ ይልቅ "ታሪካዊ" ሊባል ይችል የነበረው የኢህአዴግ መሪዎች "ከእንግዲህ በህገ መንግስቱም በም
ርጫ ህጉም የተደነገጉትን መብቶች ለመተግበር ቃል እንገባለን" ብለው ቃላቸውን ለማክበር ቢንቀሳቀሱ፣ ከዚህም በ
ተጨማሪ እስካሁን እንደታዘብነው በምርጫ ወቅት በአመፅና በህገ ወጥ ድርጊቶች የሚሰማሩት ጋጠ ወጥ የሆኑ የኢህአ
ዴግ ካድሬዎች እንጂ የህዝብ ወገኖች ስላልሆኑ ሂደቱን "ከአመፅ የፀዳ" ለማድረግ ለካድሬዎቻቸው አደብ ግዙ የምት
ል ቀጭን መመሪያ ቢያስተላልፉ እንደነበረ ግልፅ ይመስለናል። የሆነ ሆኖ ይህ ሰነድ ተፈረመ አልተፈረመ ቀጣዩ ምር
ጫ ለኢህአዴግ መሪዎች በተለይ አለም አቀፋዊ የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል ከአመፅ የፀዳ የማይሆንበት ምንም ምክንያት
አይኖርም። በቶታሊታርያን አገዛዞች ስር የሚደረጉ ምርጫዎች ፋይዳ ቢስ ሂደቶች ስለሆኑ በሰላምና በተረጋጋ ብቻ
ሳይሆን በተፋዘዘም ሁኔታ መካሄዳቸው የነበረና ዛሬም ያለ ሃቅ ነው። በመሆኑም የምርጫ ሂደት ሰላማዊና ከአመፅ የፀ
ዳ መሆን የግድ የዚህን ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ መሆን ማረጋገጫ እንዳይደለ በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል።

አራተኛው የማደናገሪያ ነጥብ የአለም አቀፍ ታዛቢዎችን የሚመለከት ነው። ይህንን በተመለከተ እንመለስ ዜና
ዊ "ካለፈው ትምህርት በመቅሰም" አዲስ በቀየሱት ፖሊሲ እነዚህ ባእዳን ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ ነበር ወይ? ለሚለው
ግልፅ ጥያቄ ገለልተኛ የሆነና ግልፅ መልስ ከመስጠት ይልቅ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የዚህ የሸፍጥ ሂደት አባሪ ተባባ
ሪ እንዲሆኑና ለኢህአዴግ አገዛዝ የተአማኒነት ሰርቲፊኬት እንዲሰጡ ሲሞክሩ እናያለን። "ምርጫው በአለም አቀፍ
ታዛቢዎች ፊት ይካሄዳል" ሲባል ብዙ ሰው ቢያንስ እነዚህ ታዛቢዎች ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያዩትን የታዘቡትን
ዘግበው የኢህአዴግን መንግስት ለማጋለጥ ይተባበራሉ የሚል ግምት እንዳለው ግልፅ ነው። ይህ ግን ፈፅሞ እርግጠኛ አ
ይደለም። ግንቦት 97 የኢህአዴግ መሪዎች በድርጅት ነፃነት፣ በፕሬስ ነፃነት ወዘተ አኳያ "ካልኩሌትድ ሪስክ" ወስደ
ው እንደነበረው ሁሉ በአለም አቀፍ ታዛቢዎች ጉዳይም እንደዚሁ "የፈለገ መጥቶ ይታዘብ" በሚል መልክ "ካልኩሌ
ትድ ሪስክ" ወስደው እንደነበረ እናውቃለን። አሁን የቀሰሙትን ትምህርት ቀስመዋልና በዚህ ጉዳይ ጨርሶ የተለየ አካ
ሄድ መርጠዋል።

አንደኛ በታዛቢዎቹ ማንነት ጉዳይ። ዛሬ የኢህአዴግ መሪዎች "የፈለገ መጥቶ ይታዘብ" የሚሉበት ደረጃ
ላይ አይደሉም። መለስ ዜናዊ መስከረም 7 ቀን በሰጠው ፕሬስ ኮንፌራንስ "መንግስታችን በዚህ በአለም አቀፍ ታዛቢ
ዎች ጉዳይ ከአለፉት የምርጫ ሂደቶች ብዙ ትምህርት ቀስሟል። በቀጣዩ ምርጫ እነዚህ ስህተቶች እንዳይደገሙ እን
ደርጋለን" ከአለ በኋላ እና ጎሜዝን በዩክሬንና ጆርጂያ ከተደረጉት "ብርቱካንና ፅጌረዳ" አብዮቶች ጋር በማያያዝ " በ
97 ምርጫ እንዳየነው የቀለም አብዮታውያን በታዛቢነት ሰበብ ሰርገው እንዳይገቡ አስፈላጊውን ማጣሪያ - ስክሪኒንግ -
እናደርጋለን።" በማለት ልክ እንደ ምርጫ ቦርዱ አለም አቀፍ ታዛቢዎቹም በተቻለ መጠን የኢህአዴግ ምልምሎች የ
ሚሆኑበትን ሁኔታ እያመቻቸ መሆኑን በግልፅ አሳይቷል።(SUDAN TRIBUNE 19/09/09)

ሁለተኛ ስለታዛቢዎቹ ተልእኮ። የኢህአዴግ መንግስት የማደናገሪያ ጥረት የታዛቢዎቹን ማንነት እኔው ራ
ሴ እወስናለሁ በማለት አያቆምም። ተልእኳቸውንም እኔው በመሰለኝ እገድባለሁ ባይ ነው። እንዳለፈው ምርጫ ታዛቢ
ዎቹ "የምርጫው ሂደት ስንኩል ነበር ወይስ ትክክለኛ? ውጤቱስ ተጭበርብሯል ወይስ የህዝብ ድምፅ ተከብሯል?" የ

ሚሉትን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች አንስተው የሚመልሱበት ሁኔታ የለም። በዚሁ ፕሬስ ኮንፈራንስ ላይ መለስ ዜና ዊ የነዚህን ታዛቢዎች ተልእኮ ለማኮላሸት ግልፅ "ቅድመ ሁኔታ" ያስቀምጣል

"ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓና ከሌሎች አካባቢዎች ታዛቢዎች የምንቀበለው በሂደቱ ላይ ብቻ እንጂ ውጤቱ ን በተመለከተ ወገናዊ አቋም ይዘው በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ እንዳይገቡ በምናቀርበው ቅድመ ሁኔታ ከተስማሙ ይሆ ናል" በማለት ስለታዛቢዎች ሚና አዲስ ፅንሰ ሃሳብ ሲሰነዝር እናያለን።

ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ አዲስ ስትራቴጂ ተቀይሷል። ባለፈው ምርጫ መለስ ዜናዊ ወዲያዉኑ "ኢህአዴግ ለቀ ጣዮቹ አምስት አመታት ሃገር ለማስተዳደር የሚበቃው መቀመጫ አግኝቷል" በማለት ከምርጫ ቦርዱ ቀድሞ ውጤቱ ን በመገናኛ ብዙሃን ማወጁና ይህንንም አካሄድ ገና አገር ያልለቀቁት አለም አቀፍ ታዛቢዎች እንዳወገዙት ይታወሳል። አሁን የምርጫው ውጤት በኢህአዴግም ሆነ በምርጫ ቦርዱ ወዲያውኑ ቆጠራው እንዳለቀ ይፋ አይሆንም። በሚገባ ለመቀመምም ብቻ ሳይሆን አለም አቀፍ ታዛቢዎቹም ከሃገር ተጠራርገው እስኪወጡ ድረስ ጊዜ ስለሚያስፈልግ ግንቦት 14 የሚካሄደው ምርጫ ውጤት በወሩ ማለትም ሰኔ 14 ቀን ይፋ እንደሚሆን ተነግረናል።

በዚህ ሁኔታና በዚህ ግንጥል ተልእኮ ተስማምተው የሚመለመሉ ከሆነ የነዚህን ገለልተኛ ተብየ ታዛቢዎ ች ተአማኒነት ከወዲሁና በግልፅ ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። ይህ ካልተደረገ ነገ "በኢትዮጵያ ሰላማዊ፣ እን ከን የለሽና ዴሞክራሲያዊ ሂደት ታዝበናል" ቢሉ ትንሽም ቢሆን በተለይ በአለም አቀፍ ደረጃ መደናገር ሊያስከትል እ ንደሚችል ግልፅ ነው። በመሆኑም "የኢህአዴግን ምርጫ ሂደት በኢህአዴግ በተመለመሉ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ታዛቢነትና በውሱን ተልእኮ" የሚለውን አካሄድ በግልፅ በመቃወም ለሚመለከታቸው ሁሉ አንደኛ ማንኛውም አካል ( ለምሳሌ የአውሮፓ ህብረት) የሚልካቸውን ታዛቢዎች ያለአንዳች ኢህአዴጋዊ ጣልቃ ገብነት ራሱ እንዲመርጥ ሁለተ ኛ የነዚህ ታዛቢዎች ተልእኮ በሂደቱ ላይ ብቻ ሳይሆን የህዝብ ድምፅ መከበር አለመከበሩን ለማመልከት በምርጫው ውጤትም ላይ አስተያየት መስጠትን መጨመር እንዳለበት ሶስተኛ ይህ ካልሆነ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት አለም አቀፍ ታዛቢ ተብየዎቹ ራሳቸውን ትዝብት ላይ ከመጣል ሌላ ምንም እንደማያተርፉ፣ እንደ ኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ ምንም አይነት ተአማኒነት እንደማይኖራቸውና ለህዝባችን የዴሞክራሲ ተጋድሎ አሉታዊ አስተውፅኦ እያደረጉ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ለማስጨበጥ መንቀሳቀስ ይኖርብናል ማለት ነው።

## 2. ስለ ምርጫና የዴሞክራታይዜሽን ትግል በአምባገነን ስርአቶች ስር

ከፊታችን የተደቀነው ዋናው ጥያቄ "ምርጫ 2002 ከተባለው ቧልት አንፃር ምን አቋም እንያዝ?" የሚለ ው ብቻ አይመስለንም። ከዚህ አልፈን በተለይ በአለም አቀፉ ሁኔታ አስገዳጅነት "መድበለ ፓርቲ ስርአት" በሚል ቅ ጥፈት በተሰማራ አምባገነን ስርአት ስር ምርጫ ሊኖረው ስለሚችለው ሚና ግልፅ አቋም ያስፈልገናል። በዚህ ጉዳይ ሁ ለት "ፅንፈኛ" ሊባሉ የሚችሉና የተሳሳቱ አቋች እንዳሉ በግልፅ ይታያል።

በአንድ በኩል የምርጫን ሚና እጅግ በማጋነን "ሁሉም ነገር ከምርጫ" በሚል አጉል አካሄድ የተሰማሩ ሃይሎች አሉ። እነዚህ ወገኖች ሌላው ቀርቶ የኢህአዴግ መሪዎች የግንቦት 97 ሽንፈታቸውን ላለመቀበልና ህዝብ የነ ፈጋቸውን ስልጣን አንቀው ለመቆየት እንዴት በሸብር ጎዳና እንደተሰማሩ እያዩም ቢሆን ህልም አለም ውስጥ የሚዋኙ ናቸው። ይህ ህልማቸው በሩ ጥርቅም ተብሎ የተዘጋበትን ዴሞክራሲ በሂደት እንገነባለን፣ ከምርጫ ምርጫ ውጤታች ንን እያሻሻልን አንድ ቀን ወደፊት ማጆሪቲ አግኝተን ስልጣንን ከወያኔ/ኢህአዴግ "እንረከባለን"፣ የኢህአዴግ መሪዎች መጀመሪያ በህዝባዊ ትግል ተሸንፈው ከመንበርከካቸው በፊት ከአሁን ወዲያ የማይመስል ነገር ነው እንጂ "በድምፅ ብልጫ" ቢሸነፉ እንኳን ይህንን በፀጋ ተቀብለው ከስልጣን ይወርዳሉ በሚል ስሌት የተቃኘ አጉል አካሄድ እንደሆነ ግ ልፅ ነው። ይህ አይነቱ ዴሞክራሲን በምርጫ ሂደት እገነባለሁ የሚለው አካሄድ ምርጫ ከዴሞክራሲ ይፈልቃል እንጂ የሌለ ዴሞክራሲ ከምርጫ እንደማይፈልቅ የማይገነዘብ በአጭሩ ምርጫ አንድ ህዝብ ለዴሞክራሲ የሚያደርገው ት ግል ሲሳካ እንደ "ድል መቋጠሪያ" የሚመጣ የድል አጥቢያ አርበኛ እንደሆነ ጨርሶ ያልተገነዘበ አካሄድ ነው። ይህ

የአድር ባዮችና ለኢህአዴግ እድሜ ቀጥል የሆነ አካሄድ ነቅቷል በሚባለው ግንባር ቀደም ሃይል ቀርቶ በህዝቡም ዘንድ ምንም አይነት ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ብዙም የምንተችበት አይደለም።

በሌላው ጫፍ ደግሞ በእንደዚህ አይነቱ የማይረባ ግርግር በምንም ደረጃ ቢሆን መሳተፍ ህዝባችንን ማታለልና "ከዋናው" ትግል ማዘናጋት ብቻ ሳይሆን "ለወያኔ መድበለ ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ በአጋዥነት መሰለፍ ይሆናል" በሚል ክርክር የተሰማሩ ወገኖቻችን አሉ። "ሁሉም ነገር ከምርጫ" የሚሉት ከግንቦት 97ም ሆነ ከቀደሙት ምርጫዎች ምንም ትምህርት ያልቀሰሙትን ያህል እነዚህኞቹ ደግሞ ከዚህ ክስተት ተማርን የሚሉት ቁምነገር የኢህአዴግ መሪዎች በምርጫ ስለተሸነፉ ብቻ ስልጣናቸውን ለህዝብ ላለማስረከብ ፈፅሞ ዝግጁ ያለመሆናቸው ሃቅ ብቻ ነው። ነገር ግን ከዚህ "ወያኔ በምርጫ አይወርድም" ከሚለው ተብሎ ተብሎ ያለቀለት ሃቅ ተነስቶ "ከእንግዲህ ምርጫ ብሎ ነገር እርም...." የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል አይመስለንም። በዚህ አካሄድ የተሰማሩ ወገኖቻችን ስለምርጫ ተሳትፎና ከዴሞክራታይዜሽን ሂደት ጋር ስላለው ዝምድና ግንቦት ትቶልን ያለፈውን ሌላ ትልቅ ትምህርት ለመቅሰም ባለመሞከራቸው ጋልቦ ግንባር ያደረሰን ፈረስ ለውጊያ ሽንፈት ተጠያቂ ለማድረግ በሚግደረደር አካሄድ የተሳትፎን ሃሳብ በጅምላና በደፈናው ሲያወግዙ እናያቸዋለን።

ታጋይ ሃይሎች በወቅቱ ሂደቱ ውስጥ ለመሳተፍ በቀየሱት ትክክለኛ ስትራቴጂ የተነሳ ግንቦት 97 ከማንኛውም በፀረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ስር ከሚደረግ ምርጫ ከሚጠበቀው በላይ ለሃገራችን የነፃነት ተጋድሎ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ ያደረገ ሂደት ነበር። ጥያቄ ውስጥ መግባት ያለበት ተሳትፎ ማድረጋችን አይደለም። ከዚህ ይልቅ መነሳት ያለበት ጥያቄ በዚህ ተሳትፎ አማካኝነት ተቀስቅሶ የነበረው በሃገራችን ከየካቲት ወዲህ ያልታየ በጎ እምርታ ለምንና እንዴት ተሰበረ የሚለው ጥያቄ ነው። ይህንን አንስተን ስንመረምር ደግሞ የደረሰው ውድቀት በምርጫው ሂደት ከመሳተፍ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ተሳትፏች ለዚህ ማእበል መቀስቀስ ወሳኝ አስተዋፅኦ ያደረገ ትክክለኛ አካሄድ እንደነበረ ስለምንረዳ ዛሬ ከግንቦቱ 97 "ትምህርት ቀስመናል" በሚል ሰበብ በ2002 መሳተፍን እንደ ከባድ ስህተት የሚቆጥሩ ወገኖች የተሳሳተ ጎዳና እንደያዙ እናያለን።

ግንቦት 97 ምርጫ በሙሉ ልብ ስንገባ ዋናው አላማችን የህዝብ ትግል ማእበል በመቀስቀስ ኢህአዴግ በሃቅም ሆነ በጭብርብር ቢያሸንፍ በምርጫው ዘመቻ ወቅት በአነገብናቸው በጎ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች ዙሪያ ህዝባችን መጭውን ምርጫ ሳይጠብቅ በዛው እምርታ ትግሉን እንዲቀጥል ለማስቻል ነበር። በምርጫው ማግስት እንደታየው ይህንን እንዳናደርግ ሁለት መሰረታዊ እንቅፋቶች ነበሩ። የመጀመሪያውና ሁሉም የሚቀበለው የሚመስለው ምክንያት ተቃዋሚ ሃይሎች ቀጣዩን ትግል ለመምራት ለዚህ አስቸጋሪ ተግባር የሚመጥን ድርጅታዊ አቅምም ሆነ የአደረጃጀት ስልት አልነበራቸውም የሚል ትክክለኛ አስተያየት ነው። ግን ይህ ብቻውን ለደረሰው ውድቀት በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም። ትግሉን በቀጣይነት ለማንቀሳቀስ የሚችል ድርጅታዊ መዋቅር (ማለትም ኢህአዴግ የማይደርስበት በህቡእ ጭምር የተደራጀ ጠንካራ ሃይል) ቢኖር እንኳን ኖሮ "ምርጫው ተጭበርብሯል፣ የህዝብ ድምፅ ተዘርፏልና ይከበር" በሚለው ቀጭን መፈክር ዙሪያ ብቻ እንታገላለን ብለን መነሳታችን ሩቅ የሚያስኬድ አልነበረም። አካሄዳችን ተአማኒነትና ቀጣይነትን በሚያረጋግጥ መልክ ተደራጅተን የህዝቡን ትግል ከጊዜ ጋር **እየደበዘዘ** ከሚሄደው "ድምፅ ይከበር" ከሚል አጀንዳ ይልቅ ከቅልበሳውና ከጊዜ ጋር **ይበልጥ እየጎላና እየከፋ** በሚሄደው የቅልበሳው መሰረታዊ ገፅታና መዘዝ በሆነው የአማራጭ ዝርፊያ ላይ አተኩሮ ህዝባችንም በዚህ የህልውና ትግል አቅጣጫ እንዲነሳሳ የሚያደርግ ጥሪ መሆን ነበረበት። ይህ አልተደረገም።

እርግጥ እዚህ ላይ አንድ የማያዋጣ ክርክር አለ። ይኸውም የኢትዮጵያ ህዝብ ለህብረቱና ለቅንጅቱ በገፍ ድምፁን የሰጠው በሰነዶቻቸው የቀረቡትን አማራጮች አንብቦና ገብቶት ሳይሆን እንዲሁ "በደመ ነፍስ" እና በኢህአዴግ ላይ ባለው ጥላቻ ተነሳስቶ "የተቃውሞ ድምፅ" (ፕሮቴስት ቮት) ለማስተጋባት ስለፈለገ ነበር የሚል በብዙ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ክርክር ነው። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች ማለት ይቻላል። አንደኛ የመሬት ጥያቄን በሚመለከት ሁለቱም ድርጅቶች ገበሬውን ከካድሬ ጢሰኝነት ነፃ የሚያወጣ ግልፅ አማራጭ አቅርበው ነበር። ይህ አማራጭ ለገበሬው "ግልፅ አልነበረም" ማለት የሚቻል አይመስለንም። ለወጣቱ ስራ አጥ፣ ለነጋዴው፣ ለኢንቬስተሩ ወዘተ የቀረቡትም አማራጮች ነገሩ ለሚመለከተው ሁሉ ግልፅ ነበሩ። ሁለተኛ ሌላም ቁም ነገር አለ። የፕሮቴስት ድምፅ ነበር ቢ

ባል እንኳን በዘመቻው ወቅት ያጋለጥናቸው የኢህአዴግ አጥፊ ፖሊሲዎች ከቀጠሉ ይበልጥ ቀውስ፣ ይበልጥ ፈተና ያስከትላሉ ብለን ተከራክረን ነበርና በአይናችን ስር እየከፉ የመጡት የህልውና ቀውሶች መሰረታዊ ምክንያት ያኔ በዘመቻው ጊዜ አቅርበናቸው የነበሩት አማራጮችም በመዘረፋቸው እንደሆነ፣ በሃገራችን ከእንግዲህ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ነፃ ምርጫ አይኖርም ሲባል እነዚህ አጥፊ ፖሊሲዎችም ይቀጥላሉ ማለት እንደሆነ እያመለከትን "አልገባውም" ያልናቸውን ነገሮች ይበልጥ እያጎላን ማስተጋባታችንንና ትግሉን በነዚህ ዙሪያ መቀጠል ነበረብን።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ በምርጫ ሂደት ተሳትፎም ጉዳይ ከአለፈው ትምህርት ቀስመን እንራመዳለን ካልን በምርጫ 97 የተደረገው ተሳትፎ ስህተት እንዳልነበረና ከዚያ ይልቅ ለደረሰው ውድቀት ተጠያቂ የሚሆነው ከሽፍጡ ማግስት ጀምሮ የተከተልነው ስትራቴጂና የአነገብነው አጀንዳ እንደነበረ ስለምናይ ዛሬ ዋናው ጥያቄ "እንሳተፍ ወይስ አንሳተፍ?" የሚለው አይሆንም። በተለይ በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው ትግል የሚያካሂዱ ወገኖቻችን በተመለከተ የቦይኮት ጥሪ ከስነልቡናዊም ሆነ ከፖለቲካ አንፃር ለትግሉ ምንም ጠቀሜታ አይኖረውም።

ግንቦት 97 ይህንን አማራጭ ስናሰላስል "ቦይኮት ከተደረገ እኛ ብቻ ሳንሆን ህዝባችንን ይዘን" የሚል አካሄድ ነበረን። "ህዝባችንን ይዘን" የሚለው አቋም የሚደረገው ቦይኮት በገፍ በሆነ፣ አለም በግልፅ በሚያየው፣ ህዝባችንም ሃያል መሆኑን በሚያሳይበት መልክ ይካሄድ ማለት ብቻ አልነበረም። በዚህ መልክ በግልፅና በገፍ ይህንን ቧልት አሻፈረኝ ከአለ በዚያው እምርታ ለነፃ ምርጫ መንገድ የሚጠርግበትን ትግል ሳያስልስ የሚቀጥልበትም ሁኔታ እናመቻቻለን የሚል እቅድ ነበረን። አሁን ከላይ በተወሳው ምክንያት ህዝባችን በገፍና በውስጥም በአለም አቀፉም ኮሙኒቲ ፊት ቀልብ በሚስብ መልክ ምርጫውን ቦይኮት የሚያደርግበት ሁኔታ የለም። ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው ህዝቡ ተገዶ ይወጣል። በየምርጫው ጣቢያ ተኮልኩሎ ረጃጅም ሰልፎች በጋዜጣም በቴሌቪዥንም ይቀርባሉ። በዚህ መልክ የቦይኮቱ ጥሪ "አድማጭ" ያጣበት ሁኔታ ምንም ላናገኝበት "የቦይኮቱን ጥሪ ህዝቡ አልተቀበለውም፣ 99% በመውጣት ለኛም ለሰከኑ ተቃዋሚዎችም ድምፁን ሰጥቶ አክራሪዎቹ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ብቸኛ እንደሆኑ ተረጋገጠ" ለሚል የኢህአዴግና የታማኝ ተቃዋሚዎች ፕሮፓጋንዳ የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጠራል። እርግጥ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ ህዝባችን ያለውን እውነታ ስለሚያውቀው ይህ ፕሮፓጋንዳ ምንም ተቀባይነት አይኖረውም። ይህም ሆኖ እንዲህ አይነቱ ውጤቱ የማይታይ ጥሪ "መክሸፉ" በህብረተሰቡ ውስጥ ትንሽም ቢሆን የተስፋ መቁረጥንና የትጥቅ መፍታትን ሂደት፣ በአለም አቀፍ ደረጃም የኢህአዴግን የተአማኒነት ጥረት ሊያግዝ ይችላል።

በፖለቲካውም መስክ ቦይኮት ትግላችንን ግፋ ቢል ባለንበት እንድንረግጥ ያደርግ እንደሆን እንጂ ቅንጣት ወደፊት የሚያራምድ አይሆንም። መጀመሪያ ነገር የፖለቲካው ምህዳር ጠበበ እያልን እያማረርን እዛው በዛው ደግሞ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታም ሆነ በሌላ ምክንያት ጥርቅም ብሎ የተዘጋው በር ለአንዷት ሰሞንም ቢሆን ገርበብ ብሎ ሲከፈት መልእክት ለህዝብ ማስተላለፍ የሚቻልበትን አጋጣሚ አለመጠቀም ትክክለኛ አካሄድ አይሆንም። እርግጥ የተሳትፎ ተቃዋሚ ወገኖች የሚያቀርቡት "ለነፃ ምርጫ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሚደረግ ተሳትፎ ለወያኔ/ኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ከመርዳት አልፎ የሚሄድ ውጤት አይኖረውም፣ ህዝባችንንም ከዋናው ትግል ያዘናጋል" የሚል ክርክር እንደሆነ እናውቃለን።

እንዲህ አይነቱ ክርክር ወንዝ የሚያሻግር አይደለም። ይህ "ከተፈራ" የመደራጀት መብት ሙሉ በሙሉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተደራጅቶ ለመታገል በህጋዊነት መመዝገብ፣ የፕሬስ ነፃነት ደብዛው እየጠፋ ባለበት ሁኔታ ባለችው ቀዳዳ ተጠቅሞ ከመንግስት ውጭ የሚሰራ ጋዜጣ ለማውጣት መንቀሳቀስ...ወዘተ አያስፈልግም እንደማለት ይቆጠራል። በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ምርጫ ተብየ ሂደት መሳተፍ ህዝባችንን ከዋናው ትግል ያዘናጋል ማለትም ሩቅ የሚያስኬድ አይደለም። እርግጥ ከፍ ተብሎ እንደተወሳው ታማኝ ተቃዋሚዎች እንደሚከራከሩት ዛሬ በሃገራችን ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ አለ ከሚል አይነቱ ስሌት ተነስተው ዘው ብለው የሚገቡበት ሂደት ህዝባችንን ለዴሞክራሲ ማድረግ ከሚገባው ትግል ሊያዘናጋ ይችላል። ነገር ግን የሃቀኛ ዴሞክራቶች በዚህ ሂደት መሳተፍ ገርበብ ተብሎ የተከፈተውን በር በህዝብ ትግል በርግዶ ለመክፈት፣ የሌለ ዴሞክራሲን አሁንም በህዝብ ትግል ለማስፈን፣ ትጥቅ በፈታ ህብረተሰብ ውስጥ ትንሽም ቢሆን አዲስ የትግል እምርታ ለመቀስቀስ ታቅዶ የሚደረግ ተሳትፎ እስከሆነ ድረስ ዘርፈ ብዙውን ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል የሚያግዝ እንጂ የሚያደናቅፍ አይሆንም። በመሆኑም ጥያቄው ተሳትፎን የማ

ውገዝ ሳይሆን በዚህ ሂደት የምናደርገው ተሳትፎ የአለፈው ስህተት በማይደገምበትና ከግንቦት 2002 ባሻገር ቀጣዩን ህ ዝባዊ ተጋድሎ በሚያግዝበት ሁኔታ እንዲሆን ምን አይነት ተሳትፎ? ከዚያስ? የሚለው መሆን ይኖርበታል።

## 3. ምን አይነት ተሳትፎ? ከዚያስ?

የተቃዋሚዎች ተሳትፎ በእርግጥ የህዝባችንን ትግል በሚያግዝ መልክ እንዲካሄድ ከተፈለገ የስትራቴጂ ያችን የማእዘን ዲንጋይ በምርጫው ማግስት ህዝባችን በቅድመ ምርጫው ወቅት ከነበረበት አስከፊ የሆነ የትግል ትጥ ቅ መፍታት አባዜ ተላቆ ለቀጣይ ትግል ይበልጥ ዝግጁ ሆኖ የሚወጣበትን በጎ አምርታ የመቀስቀስ ስትራቴጂ መሆን ይ ኖርበታል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በአንድ በኩል በምርጫው ዘመቻ ወቅት የምናነሳቸው ጥያቄዎች በሌላ በኩል ደ ግሞ በዚህ መልክ የተቀሰቀሰው ህዝባችንን እንደገና እንደ ግንቦት 97 የትም እንዳንበትነው ስለ ምርጫ ማግስት የትግል አጀንዳና ለዚህ አስፈላጊ ስለሚሆነው ድርጅታዊ ብቁነት ግልፅ የሆነ አካሄድ ይጠበቅብናል። ሁለቱን ነጥቦች ተራ በ ተራ እንመልከት።

በምርጫ ዘመቻ ወቅት ልናነሳቸው የሚገባን ጥያቄዎች በሁለት አቅጣጫ ሊቃኙ ይችላሉ።

አንደኛ ነፃ ምርጫ እንዲሆን እነዚህ እነዚህ የነፃ ምርጫ አለም አቀፍ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔ ታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል እያሉ ከኢህአዴግ ጋር ብቻ ከመደራደር ይልቅ ተቃዋሚዎች ፊታቸውን ወደ ህዝቡ አ ዙረው ያለፈውን ምርጫ ግድፈቶች እየጠቀሙ "ድምፅህ እንዲከበር ይኸ ይኸ መሆን ይኖርበታል፣ ይህ እስካልተሟ ላ ድረስ በሃገራችን ነፃ ምርጫ ሊካሄድ አይችልም" በሚለው ሃሳብ ዙሪያ እስከ መጨረሻው ድረስ ቅስቀሳ ማካሄድ ይኖርባቸዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን "ስነ ምግባር ደንብ" ተፈረመ አልተፈረመ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በዘመቻው ወቅ ት የሃቀኛ ተቃዋሚዎችን ህዝባዊ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች ማደናቀፋቸው፣ ጋዜጠኞችን ማዋከባቸው፣ የድምፅ ቆ ጠራውን ሂደት ሙሉ ቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ መንቀሳቀሳቸው አይቀሬ ስለሚሆን ይህንን ሁሉ እያነሱ የዚህን ምር ጫ ቧልትነት ማጋለጥ ይኖርባቸዋል።

ሁለተኛ በምርጫው ዘመቻ የሚደረገው ተሳትፎ ለቀጣዩ ትግል አወንታዊ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ የ ተቃዋሚዎች ቅስቀሳ ከነፃ ምርጫ መስፈርቶች አልፎ "ነፃ ምርጫ ቢደረግ ኖሮ" ህዝባችን ያገኝ የነበረውን፣ ነፃ ምር ጫ ካልተደረገ ደግሞ የሚያጣውን በግልፅ የሚያሳይ ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች አማራጭ ፖሊሲ ዎችን በማቅረብ ዙሪያ መቃኘት ይኖርበታል። ከዚህም ተያይዞ ነፃ ምርጫ በወያኔ/ኢህአዴግ ስር እንደማይቻል ሁሉ እነዚህ በቀላል ቋንቋ ለገበሬው፣ ለሰራተኛው፣ ለነጋዴው፣ ለስራ አጡ፣ ለወጣቱ፣ ለጎዳና ተዳዳሪው፣ ለከተሜው ድሃ ወዘተ የሚቀርቡ አማራጮችም መቼም ቢሆን በምርጫ ሂደት እውን ሊሆኑ ስለማይችሉ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎ ች እንደገና ደግሞ ፋይዳ ቢስ የሚሆነውን የ2007 ቡዋልት መጠበቅ ካልፈለጋችሁ ለነዚህ አማራጮች ቀጣዩን ምርጫ ሳትጠብቁ ታገሉ በሚለው ነጥብ ዙሪያ መቃኘት ይኖርበታል።

ይህ "ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል" ካልነው ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም ሁሉም እንደብሶቱ፣ ሁሉም ብሶትህ ብ ሶቴ ብሎና ሁሉም ለዘላቂ መፍትሄ ዴሞክራሲ በሚለው ጥያቄ ዙሪያ በአንድ አቅጣጫ እንዲነሳ የሚያግዝ አካሄድ ነ ው። ከፍ ብለን እንደጠቆምነው ዛሬ ለትግሉ መፍዘዝ ዋና ምክንያት ግንቦት 97 ለህዝባችን አቅርበናቸው በነበሩትና ከ ህዝባችን ድምፅ ጋር በተዘረፉት በጎ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች ዙሪያ ባለመንቀሳቀሳችንና እነዚህ በጎ አማራ ጮች ጨርሰው ከኛም አጀንዳ ከህዝባችንም አእምሮ ስለወጡ ነው። በዘመቻው በመሳተፍ እነዚህ ዛሬ ጨርሰው የተረ ሱት በጎና ህዝባዊ አማራጮች መልሰው በህዝቡ አእምሮ ማንሰራራት የሚጀምሩበትን ሂደት መቀስቀስ እንችላለን። በ ዚህ መልክ ከተሰራ እንደ ግንቦት 97 ህዝባዊ ማእበል ባንቀሰቅስ እንኳን ቢያንስ አሁን የተያያዝነውን የውድቀትና የው ዥንብር አዙሪት ሰብረን የበጎ አምርታ ጅማሮ መጫር የማንችልበት ምክንያት አይኖርም። ይህንን ማድረግ ከቻልን ደ ግሞ ምርጫ 2002 የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች እንደሚመኙት ቧልት ሳይሆን የአዲስ ትግል የመጀመሪያ ምእራፍ የሚፃ ፍበት ሂደት ይሆናል ማለት ነው።

ስዚህ ደግሞ ቅስቀሳ ብቻ አይበቃም። ከትግል አጀንዳ አንፃር ካለፈው ተምረን ይህንን አካሄድ ከመረጥን የምንቀሰቅሰውን የእምርታ ጅማሮ ለመቀጠልና ለማጎልበት አስፈላጊ ስለሚሆነው ጠንካራ፣ ቀጣይነትና ተአማኒነት ያለው አመራር ጉዳይም እንደዚሁ ካለፈው ትምህርት የቀሰመ አካሄድ መያዝ ይኖርብናል። በዚህ ጥያቄ በግንቦት 97 ማግስት በተለይ በሃገር ቤት በህጋዊ የትግል መስክ ተሰማርተው የነበሩ ወገኖቻችን ይህንን አይነት አመራር ለመስጠት ያልቻሉባቸው ምክንያቶችና ከነዚህ ስህተቶች ስለምንቀሳማቸው ትምህርቶች ህብረቱ "ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ስንል" ብሎ ባወጣው ሰነድ በሰፊው ለማብራራት ተሞክሯል። እነዚህ ስህተቶች የሚታረሙበትን ሁኔታ ከወዲሁ ካላመቻቸን አሁንም በምርጫ ዘመቻ ወቅት ሊቀሰቀስ የሚችለው እምርታ የሚከስምበትና ለትግል የተነሳሳው ህዝባችን መልሶ በተስፋ መቁረጥ ባህር የሚዋኹቅበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

ይህ እንዳይሆን ከፈለግን ለጊዜው በሁኔታው አስገዳጅነት በሃገር ውስጥ ባይቻል ቢያንስ በውጭ አገር ያለው ዴሞክራትና አገር ወዳድ ሃይል ተደጋግሞ የተደረገውን የሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጥሪ ከምርጫው በፊት ተግባራዊ በማድረግ አንድ የጋራ ስትራቴጂና የጋራ ታግሎ አታጋይ አካል የመፍጠሩን ጉዳይ ዛሬ ነገ ልንለው አይገባም። የዚህ ጉባኤ ተግባር ቀጣዩን ምርጫም ሆነ አጠቃላዩን የዴሞክራታይዜሽን ትግል በተመለከተ በአለም አቀፍ ደረጃ ስለሚደረገው ትግል ስትራቴጂ አውጥቶ ያንንን በመተግበር የሚወሰን አይሆንም። በሃገር ውስጥም ቢሆን በአንድ በኩል በተቀየሰው እቅድ አማካኝነት በምርጫ ዘመቻው ወቅት ህዝባዊ እምርታ ለመፍጠርና ከግንቦት 2002 በኋላም ይህ እምርታ ቀጣይነት እንዲኖረው ለመስራት ለሚፈልጉ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ስብስቦች ድጋፍ የሚያቀርብበትን ዘዴ በሌላ በኩል ደግሞ ለዚሁ አላማ በህቡእ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ሊፈጠሩና ሊጎለብቱ የሚችሉበትን ሁኔታ አጥንቶ የመተግበርም ሃላፊነት ይኖርበታል። ይህ በራሱ እጅግ ሰፊ የሆነና ወሳኝ የትግላችን ገፅታ እንደ መሆኑ መጠን ሌላ የመወያያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሰፊ የሃሳብ ልውውጥ የሚያስፈልገው ስለሆነ ወደፊት እንመለስበታለን።

ህዳር 2002 ዓ.ም.